ፈንገጡና በዚህም የወያኔንና የጠረኞችን ስትራቴጂ በማገዙ ነው:: በመሆኑም ይህንን ሂደ
ቱን ሙሉ በሙሉ ለማጋለጥና ክፍፍሉ በአንድ በኩል ከጋራ ዓላማችንና ራእያችን አፈንግጠው
ለዚህ ማፈንገጣቸው እንዲመች ብቻ በስንት ድካም የተገነባውን ህብረት ለማፈራረስና ለማዝ
ረከረክ ከወያኔና ከጠረኞች ተባብረው በሚሰሩ ኃይሎችና በሌላ በኩል ደግሞ በጋራ አቋምና
በዲሞክራሲያዊ ተቃውሞዋቸው ጸንተው በቆሙ ኃይሎች መሃከል እንደሆነ ለማሳየት ያላሰለሰ
ቅስቀሳ ለማድረግ ወስነናል:: / የሚቀጥለው አርብ በዚህ ጉዳይ አንድ ጓድ በቀስተደመና
ሬድዮ ቃለ ምልልስ ያደርጋል/

2ኛ/ ይህንን የሦስት አገጣጫ የሚሰነዝር ኢተፖድሀንም ሆነ ዲሞክራሲያዊ ትግሉን
ለማዝረክረክ የሚደረግ ዘመቻ ከሁሉ በተሻለ አመቺ ሁኔታ ለመቋቋምና እስከ ግንቦትም ሆነ
ከግንቦት በኋላ የህብረቱን ህልውና ለማረጋገጥ ያለው አንድ አማራጭ ዲሞክራሲያዊው የተቃ
ዋሚ ሰፈር በጋራ አቋሙ፣ በአደረጃጀቱም ሆነ በፋይናንስና በማቴርያል አቅሙ ከፍራንክ ፈር
ርት ስብሰባ በፊት ጀምረን የምንመኘውን እመርታ ለማምጣት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ እንደሆ
ነ ከመቼውም ይበልጥ ግልጽ ሆኖልናል::

በዚህ በተለይ ለህድረ ግንቦት ትግል የሚቀየሰው ስትራቴጂያችን ውስጥ አዲስ አበባ
ያሰብነው አገር አቀፍ ጉባኤ ትልቅ ቦታ ስለሚኖረው ያለንን አቅምም ሆነ ጉልበት በሚመጡት
ወራት በሱ ዙሪያ ለማዋል ወስነናል::

## 2. የጉባኤው ዓላማ

ሀ/ አሁን በመነዛት ላይ ያለው ውዥንብርና ጸኑ ዲሞክራት የሆኑ ተቃዋሚያች በአን
ድ ድምጽ የመናገርና የመንቀሳቀስ አለመቻል እስከ ግንቦት ድረስ ባለው ጊዜ ለወያኔ፣ ለሻ
ማ ያዥያችና ለጠረኞች ብቻ የሚያመች አደገና ሁኔታ በመፍጠሩ በኢተፖድሀ ሰነድ የጸኑ ድር
ጅቶችና በተቻለ መጠን ከየአካባቢውና ከየምርጫ ጣቢያው የሚመጡ ግለሰብ ተወዳዳሪያች፣ የሲ
ቪክ ስብሰቦች ተጠሪያች፣ የታወቁ ዲሞክራት ምሁራንና ከተቻለም የተወሰኑ የሃገር ሽማግሎች
የሚገኙበት የሃገራችን ዲሞክራቶች በአንድ ቋንቋ የሚናገሩበትን ስትራቴጂ መቀየስ፣

ለ/ በጉባኤው ፍጻሜና በምርጫው ቀን መሃከል ባሉት ወራት ይህንን በኢተፖድሀ ሰነ
ድ ዙሪያ የተነደፈ ስትራቴጂ ይዘው ተሳታፊያች ሁሉ ወደየመጡበት እየተመለሱ በህዝቡ ውስጥ
ቅስቀሳ እንዲያደርጉ የሚያስችል አቅድ ማውጣት፣

ሐ/ ከጉባኤው ተሳታፊያች መሃል ከኢተፖድሀ አባል ድርጅቶችና ከሌሎችም የተውጣጣና
ቢያንስ በከልል ደረጃ መዋቅር ያለው 'አገር አቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ' ማቋቋም፣

መ/ ይህ ኮሚቴ እስከ ግንቦት ያለውን ትግል ማስተባበር፣ የምርጫው ጊዜ ሲቃረብም
እንደገና ተሰብስቦ ሁኔታውን በመገምገም ስለተሳትፎም ሆነ ስለቦይኮት የመወሰን ሃላፊነት
ብቻ ሳይሆን በህድረ ግንቦት ወቅት ስለሚደረገው ትግል አንድ የጋራ ስትራቴጂ የመቀየስ ሃ
ላፊነት ይኖረዋል::

## 3. የጉባኤው ዝግጅት

ሀ/ ዓላማው በተቻለ ከየከልሎችና ከየምርጫ ጣቢያዎች የተመረጡ ተወዳዳሪያችን የማ
ሳተፍ ዓላማ ቢሆንም ይህንን ማድረግ እጅግ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል:: ለማንኛውም ያሉት
የምርጫ ከልሎች 560 ገደም ስለሆኑ ተወዳዳሪያችንም ሆነ ሌሎችን ተሳታፊያች ጨምሮ እንድ
600 ሰው ያህል ለሰስት ቀናት ለመሰብሰብ ታርጌት ማድረግ ያስፈልጋል:: ከየምርጫ ከልሉ
በሙሉ ሰው ካልተገኘ ከሱ የሚጉድለውን የሌሎች ተሳታፊያችን ቁጥር በመጨመር ኮምፕንሴት ማ

ድረግ ይቻላል::

ሀ/ በዚህ ጉባኤ የሚሳተፉ ሁሉ ሰመረጡ ከጉባኤው ባሻገር እስከ ግንቦትም ሆነ ከግንቦት በኋላ በጋራው ትግል ለመሳተፍና ለመቀጠል ፈቃዱም ሁነ ችሎታ እንዳላቸው፣ በጽኑም ዲሞክራሲያዊ አቋም የታወቀ መሆን ይኖርባቸዋል:: ምርጫው ካምፔይን ለመሳተፍ የተዘጋጁ ድርጅቶችም ሆኑ ግለሰብ ተወዳዳሪያቸ ምርጫው ሲቃረብ እንደገና ሁኔታው ተገምግሞ የመሳተፍም ሆነ በይኮት የማድረግ የጋራ ውሳኔ ሲወሰድ ይህንን ውሳኔ ለማክበር ከወዲሁ ቃል መግባት ይኖርባቸዋል:: ይህ ካልሆነና የጉባኤውን ውሳኔ ትቶ ሁሉም የራሱን አጀንዳ የሚያራምድበት ሁኔታ ከተፈጠረ ትርፋችን ኪሣራ ብቻ ይሆናል:: ለህድረ ግንቦተ ትግልም ለከ አሁን የምንገኝበት የውዥንብር ሁኔታ ውስጥ እንወድቃለን::

ሐ/ ስብሰባውን ጥር መጨረሻ ላይ ለማድረግ መዘጋጀት ያስፈልጋል:: ይህም የሚሆነው የእናንተን 'ይቻላል' የሚል መልእክት አግኝተን ሃሳቡን ይፋ በማድረግ ላሰብነው ፈንድሬዚንግ ጊዜ ለመስጠትና ከጉባኤው በኋላ ደግሞ እስከ ግንቦት ድረስ ቢያንስ የሁለት ወራት ቀስቀሳ ለማካሄድ ጊዜ እንዲኖረን በማሰብ ነው::

መ/ ዝግጅቱን ለመጀመር ከኢተፖድህ የሃገር ውስጥ ጽ/ቤትና ከሴክሬታርየቱ ጋር በቅርብ እየተገናኘ የሚሰራ አንድ ጊዜያዊ ኮሚቴ ባስቸኳይ ማቋቋም ያስፈልጋል:: ለጊዜው የሃገር ውስጥ ጽ/ቤቱ ጉዳይ የተዘረከረከ ስለሆነ በእናንተ ዙሪያ አርግጠኛና አስተማማኝ የሆኑና ለሥራው ብቃት ያላቸው ግለሰቦችን የሚያካትት ይፋ ያልሆነ አካል መፍጠር ያስፈልጋል / በዚህ ጉዳይ እነ አካሉ፣ ታሪኩ ወዘተ ጋር መመካከር ይቻላል::/ ለማንኛውም ግን ነገሩ በጣም ባስቸኳይ መጀመር አለበት:: ምናልባት ይፋ የምናደርገውና የፈንድሬዚንግ ዘመቻም የምንጀምረው — ውጭ ባለው ኢትዮጵያዊ ዙሪያ — ዲሴምበር 18/19 ከታሰበው የኢተፖድህ ስብሰባ ጋር አያይዘን ሊሆን ስለሚችል ስለአጠቃላይ ሁኔታው ግልጽ ስእል ለማግኘት ብዙ ጊዜ የለንም::/

## 4. የጉባኤው ማዘጋጃ በጀት ጉዳይ

ሀ/ የበጀት ጉዳይ ከተነሳ አሁን በዚህ ፕሮጀክት አካባቢ መሰብሰብ ያለበት ገንዘብ ለጉባኤው ዝግጅት ብቻ የሚሆን አይደለም:: ከጉባኤው በኋላ እስከ ግንቦት፣ ከግንቦትም በኋላ ላለው ቀጣይ ትግልም አብሮ ማሰብ ያስፈልጋል:: ኢተፖድህን ስናቋቁም ለቀጣዩ ትግል አምስት ሳንቲም ሳንይዝ ስለነበረ ይህ አቅም ማጣት የተፈጠረው ዲናሚክስ እንዲቀዘቀዝ የማይናቅ አስተዋጽአ አድርጓልና ይህ ስህተት መደገም የለበትም:: እናቋቁመዋለን የምንለው አገር አቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ እስከ ግንቦትም ሆነ ከዚያ በኋላ ለሚያደርገው እንቅስቃሴው የቢሮ ማቴርያል፣ የሰው ኃይል፣ የመንቀሳቀሻና የሌላ ሥራ ማስኬጃ አቅም ያስፈልገዋል::

ለ/ ይህ ፋይናንስ ከየት ይመጣል? ግራፒክ ለዚህ ስብሰባ የተለየ በጀት አይኖረውም:: ነገር ግን ከቀስተ ደመና በጀት በተጨማሪ ለ1999/2000 አመራሩ ከሚመድበው በጀት 150ሺ የኢትዮጵያ ብር ለጉባኤው ዝግጅት ለማዋል ባለፈው ሳምንት ስብሰባው ተስማምቷል

ሐ/ ይህ በጀት "በተባባቂነት" የሚመደብ ነው:: ለስብሰባው ማዘጋጃና ለቀጣዩ ትግል የሚያስፈልገውን በጀት በውጭ ካሉ ኢትዮጵያውያን ዙሪያ ለመሰብሰብ የፈንድሬዚንግ ካምፔይን ለማድረግ ሃሳብ አለ:: እስካሁን ካነጋገርናቸው ጥቂት ሰዎች ለእንዲህ ዓይነቱ ፕሮጀክት ተለቀ ድጋፍ ያለ ይመስላል:: በዚህ መልክ የሚሰበሰበው ገንዘብ ለጉባኤው ማዘጋጃ ከበቃ ግራፒክ ቃል የገባው ገንዘብ ለቀጣዩ ትግል ለማዋል ይቻላል ማለት ነው::

ይህ በጀት ለቀጣዩ ትግል /ለሚፈጠረው አስተባባሪ ኮሚቴ ወዘተ/ እንዲውል ከተ
ፈለገ ከዲሞክራትና አገር ወዳድ ወገኖች በቂ ፈንድ ማግኘት ይኖርብናል:: ስለዚህ በውጭ
ላለው ኢትዮጵያዊ ኮሙኒቲ አሳማኝ የሆነ ፕሮጀክትና የድጋፍ ጥሪ ባስቸኳይ መሰራጨት ይኖ
ርበታል:: ይህንን ለማድረግ አዘጋጅ ኮሚቴው በአስቸኳይ ተቋቁሞ አንዳንድ ዝግጅቶችን ካ
ደረገ በኋላ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ዲሴምበር 18 ስብሰባ ተከትሎ ይፋ ጥሪው መተላለፍ
ይኖርበታል::

የዚህ ጥቅሙ ገንዘብ መሰብሰቡ ላይ ብቻ አይደለም:: አሁን ባለው ውዠንብር ገራ
የተጋባውን ዜጋ መልሰን ግልጽ የሆነ ፔርስፔክቲብም ልንሰጠው ስለምንችል ቀጣይነት ያለው
ዳይናሚክስ ለመፍጠርም የሚያስችለን ፕሮጀክት ነው:: ነገሩን ከዚህም አንጻር ማጤን በጣ
ም አስፈላጊ ነው::

ከቻላችሁ ዊክኤንዱ ላይ ተሰባስባችሁ በነጥብ በነጥብ ተነጋገሩና በጣም ባስቸኳይ
/በሚመጣው ሳምንት ውስጥ/ አንድ ፋክስ አርጉልኝ::

25/11/99